THE JOURNEY

LIFE 101

EDITION - 9



FREE COPY

PHOTO COMIC BOOK DEVELOPED BY:

Editorial

Abiy Alazar
Sofnias Nega
Professor Tsige G/Mariam
Dr. Daniel Fekade
Dr. Sori Ararsa
Dr. Endale Workalemahu
Dereje Tesfaye

Production Team

Ashenafi Hadera
Mack Eshete
Leykun Tesfaye
Natenael Wakejiera
Yordanos Kassahun

Graphic Design, Layout and Script writers

Henok Abinet
Scriptwriter: Fikru Kassa
Graphic Designer: Mack Eshete

Mare Zenebe
Scriptwriters: Zewge Abate &
Biniyam Wubishet
Supporting Scriptwriter: Daniel Seleshi
Graphic Designer: Tsigereda Abay

Bilen & Yonathan
Scriptwriter: Biniyam Wubishet
Graphic Designer: Pascal Funder

Sammy Girma
Scriptwriter: Zewge Abate
Supporting Scriptwriter: Addis Tesfa
Graphic Designer: Tsigereday Abay

Cover Concept and Design

Mack Eshete

Consulting Team

Andrew Whaley (Story line development)
Suleiman Shifaw (Art Direction)

Main Cast

Assamenew Demessie as Yonathan Urgessa
Nebiyou Abera as Henock Abinet
Netsanet Mesafint as Bilen Teferra
Sossina Belete as Mare Zenebe
Temesgen G/Egziabher as Sammy Girma

Supporting Cast

Messay Girma as Natnaiel (Natti)
Yohannes Damte as Taddese
Alemayehu Belayneh as Tariku
Rekik Teshome as Emmy
Maria Daniel as Sofia
Henok Birhanu as Matti
Marta Taye as Mahlet
Aman Asfaew asYafiet
Aster Derebew as Rekik
Ermiyas Zeynu as Binyam
Ermias Eshetu as Mike
Asfa Berhanu as Ato Abent
Tameru Selman as Zekarias
Million Aragaw as Fistum

Special Thanks to:

Tena Hotel

MEET THE KIDS OF 'LIFE 101'!

Welcome to 'Life 101,' a long running photo story book which follows the lives of five fictional Addis Ababa University students.

If you missed the eighth edition of 'Life 101,' here's the story so far.....



ዮናታን ከሻሸመኔ ኮንሰርት ተመልሷል። ብሌን ስለ ግንኙነታቸው ማውራት እንዳለባት እምና ዮናታንም ጥፋቱን በፍትር ጨዋታ ለመካስ እስበው ቢገናኙም የሪቲት በቦታው መገኘት ሁሉንም ነገር አበላሽቶት ብሌን ጥላቸው ሄዳለች። ይህ አለመግባባት ወዴት ያመራ ይሆን?



እነ ኤሚ የማራን አለባበስና ቁንጅናዋን አጉልቶ ለማውጣት ከፍተኛ ጥረትና እንክብካቤ ሲያደርጉ በሌላ በኩል ደግሞ ታሪኩ ይህን ተግባር ሲያወግዝ አሷ ይባስ ብላ ሞፈራ ቤት መሄዷን እንዲሁም ሁኔታውን መውደዷን ተከታትለናል ቀጣዩ ታሪክ በዕትም 9 ቀርቧል።



ሄኖክ ለአረፍት አዋሳ ሄዶ ነበር። አባቱ በእሱ ላይ ያላቸውን መተማመን አይታል። በዚህም በሞልፈሰስ መሆኑ አናዶታል። ከአሪያስ የተባለ አብሮ አደግ ጓደኛውም ኤችአይ ቪ ፖዝቲቭ መሆኑን አውቋል። ይህም ስለራሱ እና ስለጓደኛው የበሰለ አንዲያስብና እንዲጨነት መነሻ ሆኖታል። በዚህ መነሻ ጓደኛውንም ለመርዳት እየተሯሯጠ ነው። አርስቶ ከገባበት ሞንቶትና መደናገጥ እንዴት ይወጣ ይሆን?



ላሚ ማህሌት ላይ ፍላጎት ካሳየ ቀን ጀምሮ ጓደኞቹ እንዲያወጣት እየጎተጎቱት ነው - ባይቀበለውም። ከማሂ ጋር ወደነበረው ቀጠሮ ሲሄድም ይቺን ቀን ማለፍ የለብህም ብለው አበረታትተውታል። ሲመኛት የነበረችውን ማሂ አግኝቶ ሲስማት እና ሲተሻሻት ejaculate በማድረጉ ደንግጧል! አፍሯልም። ወደ ዶርሙም ሲሄድ ላያገኛት ወስኗል። ላሚ በቃሉ ይገኝ ይሆን?

This comic book was supported by Cooperative Agreement Number U62/CCU324877 from CDC. Its contents are solely the responsibility of the authors and do not necessarily represent the official views of CDC. All characters and stories in this comic book are fictional and are not in any way represnting real life people, departments, or faculties at Addis Ababa University.

HOW TO READ YOUR 'LIFE 101' PHOTO STORY BOOK

INSTRUCTIONS:

STEP 1:

Examine the pictures first on a superficial level. Most of the story will actually be told through the graphics. Notice the characters, what they are wearing, the setting and any action being depicted. This will fill in some of the details left out of the text.

STEP 2:

Read the captions from left to right and top bottom. Captions are used for narration purposes that describes what is happening, where and when.

ሄናኒ ማሬን ወደ Main ካፌ አካባቢ ይዟት ይሄዳል።

STEP 3:

Read the pictured panels in order of the numbers written on the upper left corner. A panel is an individual frame ordered in sequence of photos in a storybook or comic book. A panel consists of one photo that depicts a single moment and can help indicate the flow of the story.



STEP 4:

Speech balloon and thought bubbles are devices used to indicate dialogue. Bubbles are read in the order from the highest bubble to the lowest. Left to right.



Speech balloons indicate words spoken aloud

Thought bubble convey subjective thoughts

ENJOY!!


በቃ!!!???


ሚጢጢዬ ቅናት
1
ይደብራታል ብሎ አያስብም
ከሷ ጋር ሆኖ ያን ያህል ሲዘጋኝ?
እንዴት
ነው ደሞ የምታየው?
ትንሽ እንኳን
አታፍርም?


2
የሆነ ነገርማ አላቸው።።
ይሄ ሁሉ መቀራረብ ዝም ብሎ
ይመጣል?


3
በዚህ semister break
አወስናለሁ።። ወይ መቀጠል
ወይ ማቆም...


ስልኩን አንሺው!
4
እሺ መደወል ነበረብኝ
አልደወልኩም።።
ዝም ብላ ታካብዳለች?


5
ከኔ ጋር አልሄድሽም
ብዬ አልጨቀጨኳት!
...Class ጨርሳለች።።
ስልኳን ለምን
አታነሳውም?


ሰሞኑን ተቆልላለች።።
አሁንም በረቂቅ ጠርጥራኝ
ከሆነ ይገርማል!
6


አስቻለሽ ወይ?
7
ሰሞኑን የምተኛው እንቅልፍ!? ሙቀቱ ነው መሰለኝ
ወይ እንቅልፍ! አንቺ ደልቶሻል።
8
የዮኒ መምጣት እንቅልፍ አሳጣሽ? ኪ ኪ ኪ እንዳውም ደወለልሽ አንሺው።
ባክሽ ተይው! ወሬያችንን ሊያቆረፍድ።
RING
9
ትቀልጃለሽ! አንሺው እንጂ! ... ሰላም አይደላችሁም እንዴ?
ሳይሆን አለ አይደል? ... ትንሽ break ነገር ሳያስፈልገኝ አይቀርም...
10
የምን break ነው የምታወሪው? እናንተን የመሰለ couple ቀርቶ ሌላውም አብሮ ይኖራል።
እኛን የመሰለ!... ውስጣችንን ማን አየ!?
በዛ ላይ break ማድረግ መፍትሄ አይደለም... ሽሽት ነው።
11
እና በቃ አታነሺውም? አንቺ ደግሞ እልህሽን መቼ መተው እንዳለብሽ አታውቂም።
ግን የእውነት እየሸሸሁ ነው? ለዚህ relationship በቂ አልሞክርኩም?
የጓደኞቹ ጨዋታ
12
...relationship ብለህ ከያዝከው ማድረግ ያለብህን ማድረግ፤ ለሷም በቂ ግዜ መስጠት አለብህ።
ቆይ አንተ ስጠፋ ለምን አትጮህብኝም?
13
እየቀለድክ ነው አይደል? የፈለገ ጓደኛህ ብሆን ከሷ ጋር ታወዳድረኛለህ? ነው ወይስ ሳላውቀው ካንተ ጋር relationship ውስጥ ነኝ?
14
ቀልደህ ሞተሃል! ሰሞኑን ስለተደባበርን ነው እንጂ እኛ እኮ በደንብ አንገናኛለን...
15
አንደኛ የሚሰማህን ነገር በደንብ ማውራት አሳፈሞ የልባፈን እንድትነግርህ ማድረግ አለብህ።
አሺ የኛ relationship therapist ሙት ከነመላጣህ Dr. Phill


16
I am serious. እዚህ ግቢ ብሉን ትወደዳለች
... ስንቱ መሰለህ አጣብሰኝ የሚለኝ? ይህን ሁሉ pressure ተቋቁማ ነው ካንተ ጋር ያለችው::
ኧረ ባክህ? እኔስ pressure የለብኝም? ... ዋናው ነገር space አላጣችኝ::
17
space?! በሳምንት ሁሉቱ ያውም በወጉ ሳታዋራት ስለ space complain ታደርጋለህ?
18
Ya! እኔ ከሷ ጋር Chill ማድረግ እንጂ ሪፖርት ማቅረብ አለብኝ?
የት ነህ? ምን አደረክ? ፕሮግራምህ ምንድነው?.... በገዛ እጁ እስር ቤት!?
19
እስክ ዛሬ ከያዝኳቸው ቺኮች ቢ. matured እና አላማ ያላት ልጅ ነች::
አሁን ምን አድርግ ነው የምትለኝ?
ወንድ አይደለህ!? አትፍራ አግኛት::
20
ስራህን እያወቅክ? አስቲ አሁን ደውልላት
ቅድም እኮ ስደውል ይጠራና ይዘጋል... ቆይ ይጠራል...
21
አይገርምም ተዘጋ!
እንደገና ደውል! network ይሆናል::
22
THE SUBSCRIBER'S PHONE YOU HAVE DIALED IS SWITCHED OFF
23
ጭራሽ switched off!? ለዚህማ ማን ብሎን! አልህዋን ነው የማስጨርሳት...
24
ስልኩን መዝጋት አልነበረብኝም?
ላብራውና እና.. ሪች ምንም ከሌላት ላግኛት::
25
RING RING RING RING RING RING RING RING
ሃይ!
26
ስደውልልሽ አታነሽም! ጭራሽ ዘጋሽው!!
አይ የማይመች ቦታ ሆኜ ነው::
27


28
ታዲያ አትደውይልኝም?... ሰሞኑን ልክ አይደለሽም... ምን ሆነሻል?
29
እኔ ነኝ ልክ ያልሆንኩት!?
ታዲያስ! ማመናጨቅ ... ስልክ ማጥፋት... ባለፈውም ሰው ፊት ብድግ ብሎ መሄድ... ምን ይሉታል?
30
ብኖር ባልኖር ምን ለውጥ አለው?
31
ነግሬሻለሁ አንቺን አስተዋውቅሻለሁ እንዳልኳት!!.. ታዲያ በመምጣቷ ምን እንደዛ ያስደርግሻል!?
32
እሷን ተዋት! ... አንተ ግን ተለውጠሃል... ለመገናኘት initiative የምወስደው እኔ ብቻ ነኝ::
33
እና አንቺ ዝም ብትይ እኔ የማልደውልልሽ እና የማላገኝሽ ይመስልሻል? እንደዚህ ማሰብሽ ይገርማል!
34
ቆይ! አንተ ግን ሪሌሽንሺፓችን ትክክል ነው ብለህ ነው የምታምነው?
35
ማለት... perfect አይደለም... ግን ትልቅ ችግር የለብንም... በርግጥ ሰሞኑን ትንሽ ለውጥ አይቼብሻለሁ::
ለማንኛውም እኔ ብቻዬን መድረቅ ሰልችቶኛል...
36
ስለዚህ እኔን blame እያደረክ ነው?
37
No!
38
እኔ እኮ ብቻዬን የምትይው ነገር ነው ያልገባኝ::
39
ልክ ነህ አይገባም!
40
የምናወራው አማርኛ... መግባባት እኮ አቃተን..
41
ካቃተን ታዲያ... why don't we take a break?
ማለት!? do you think that this is the solution?
42
Ya!
43
TO BE CONTINUDE ...


የዘፈን ዳርዳሩ...


ማሬና ሃይማኖት White House
1
የዶርም ልጆች ተስማምተውሻል የኔ ምቹ እርስ በርስ ይጨቃጨቃሉ፤ እቃም ይሰራረቃሉ መሰለኝ።።
ወይኔ ጉበሰ ናቸው እንደውም እኔን መነጠል አይፈል ጉም።። ጥሩ ልጆች! በቃ እህት ማለት ናቸው።።


2
ታድለሽ! ይህ አድል ይጠይቃል።።
ትናንት የት እንደወሰዱኝ ታውቂያለሽ?


3
የት ወሰዱሽ?
የሆነ ቤት መስደው ..አሰሜን ሲያሳዩኝ አመሸ።። በስማም! ስንት አለም አለ መሰለሽ የሙዚቃው ብዛት፤ የሴቱ አለባበስ...


4
አዩ ያንቺ ነገር ጭፈራ ቤት ሄደሽ ነው?
ብታይ ደስ ይላል ኤሚ እውነቷን ነው አለም ሰፊ ናት አለምሽን በወጣትነትሽ ቅጭበት የምትሰሙ።።


መዝናናቱ ጥሩ ነው ።። ግን ለMid ምን ያህል ጊዜ እንደቀረሽ ታውቂያለሽ ?
5
ባክሽ ማወቁ አይከፋም።። ወንዶቹ ደግሞ አፍጠ ውበኝ ነው ያመሹት ።።


6
ማሬ በሌላ እንዳታይብኝ ጊዜሽን አስተውለሽ ተጠቀሚበት ማለቴ ነው፤ እንደውም ከስዓት ኩኔዲ እንግባ።።
ሃይሚ ሰኔ ብለሽ እንደሆን ይጾፍሻል።።ሁሉን ነገር ተጠንቅቄ ነው የማረገው፤ ጥሩ ሀሳብ! ጉበተን እናንሳሳ።።


እነ ኤሚ ባር ውስጥ
7
ሃኒያችንን አየሻት አይደል? እንዴት ወንድ ሁሉ ሰፍ እንዳለባት?
ልጅቷ እኮ potential አላት።። ምን ዋጋ አለው ያ ገጣማ የአገሯ ልጅ እያለ!?


አሱን ተይው ባክሽ! ከኛ ጋር ስትሆን ብዙ ነገር ስለምታይ ከነመፈጠሩም ትረሳዋለች።። ደግሞ easily የምትለወጥ ልጅ ናት።። Mood ቶሎ ይጣታል።።
ምን እንደገረመኝ ታውቂያለሽ? አረማመዷ፤ ንግግሯ፤ ባንዴ መቀየሩ
8


እኛስ ቀላል ደክሞን ያንን ሻርፕ ለማስጣል? አሁን የጫማ መጥረጊያ ልናደርገው...
9
By the way የሱዛን ስልክ ዝግ ነው። እሷም ጠፋች?
ታውቂያት የለ ሲደብራት?


ማሬ ወደ ኬኔዲ ላይብረሪ ስትሄድ
10
እሺ አንቺ አመፀኛ!
11
በስማም እንዴት እንዳስደነገጥኸኝ


እንዴት ነው የልብሽ ደረሰ?
12
አራት በላን ተጫወትን ከዛ ተመለስን ምን ማለት ነው የልብሽ ደረሰ ማለት? ከነሱ ጋር ስለወጣሁ ነው?


13
ማሬ እነዚያን ጭራቆች አታውቂያቸውም የስንት ፍሬሽ ህይወት እንዳበላሹ... ሰው አግኝተሽ ሞተሻል?
ራሴን የማውቅ ልጅ ነኝ። መስሎህ ነው እንጂ ያን ያህል መጥፎ ልጆች ደሞ አይደሉም።


14
ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው። ለየትኛው ሽማግሌ ነው የሚያሰለጥኗት እየተባለ ግቢ ውስጥ ሲወራ ስምሽ እንዳይጠፋ ስጨነቅ...
ታውቀኝ የለ! እኔ እንደዛ አይነት ሴት አይደለሁም። ምንም ቢወራ አትጨነቅ


15
በይ አሁን እቸኩላለሁ አክስቴ ጋር ልሄድ ነው semester break ከገባ ጠይቂያት አላውቅም። በኋላ ከዚህ ስመለስ አራት እንበላለን።
እሺ!
እሱ እስኪመጣ በደንብ ካነበብኩ በቂ ነው።


Later in the evening
16
ምነው ተዳከምሽሳ ብይ እንጂ!
እየበላሁ ነው! ለነገሩ በጣም ደክሞኛል።
በቀን ሁለቴ ልብስ መቀየር ተጀመረ እንዲህ ነው መሸሻል!


17
እሱማ እንዴት አይደክምሽ ስታረጠረጭ አድረሽ?
ወይ ታሪክ! አንተ ደግሞ ጓደኞቼ ጋር ተዝናናሁ አለቀ ሴላ ምን አለው?


18
ምን አለው? ሲነግሩሽ አትሰሚም... ና ማክህ! አንድ ጅን አምጣልኝ::


19
ማሬ እኔ እኮ ፊት ለፊት የምነግርሽ ለክፋት አይደለም ስለማስብልሽ ነው:: ስለትምህርትሽም ስለእኛም እንድታስቢ እፈልጋለሁ::


20
ለሐርግዋ ለክፋት ብሎ እንዳልሆነ ይገባኛል:: ስለሚወደኝ ነው:: ግን ቢመደኝም አይነት አለው...
ይገባኛል! አሁን ግን እየመሸ ነው አንሄድም?


21
Class ይዘን በደንብ ማውራት አለብን!
ታሪኩ ምን ነካህ? ተነጋግረን!


22
ምን እናርግ አልኩኝ... እናወራለን እቅፍ አድርጌሽ እተኛለሁ


23
ቅድሙኑ ልጋብዝሽ ሲለኝ እሺ ባላልኩ አሁን እምቢ ብል ይደብራል:: አንድ ነገር ቢያረገኝስ!
እሺ በቃ ጠጣ ጠጣ አርግና አረፍ እንድንል...


Later on
24
ደስ ይበለው ብዬ የፈለገውን ባረግም አኩርፏል::
ይኸውልሽ ከአሁን በኋላ ቀጥ ለጥ ብለሽ ትምህርትሽን ትማሪያለሽ::


25
አሁንስ እየተማርኩ አይደል ምን ለማለት ፈልገህ ነው?
እነዚህ ጓደኛ ተብዬ ዝተቶችሽን ወደዛ አስወግጂሽ የመጣሽበትን አላማ ጠብቂ::


26
እንዲህ አትበል! ሰው ስለማያውቀው ነገር ሲያወራ አያምርበትም::
እኔ ሳላውቅ አንድ ቦታ እንዳትሄጂ! ተናግሬያለሁ በቃ::


27
ጌታ የሰጠኝን ፍቅር ለመንጠቅ! እስቲ አሁን ምን አረኪቸው ምናለ እሷን ቢተውልኝ?


28
ማሬ እና ታሪኩ ማታ ወደ ግቢ እየገቡ
ሃይ honey! እንዴት ነሽ... በሽ ሆንሽ አይደል እንዴ ሰሞኑን!


የት እሄዳለሁ ብለህ ነው:: ተዋወቀው ጓደኛዬ ነው::
ታሪኩ ይገለጥ እባላለሁ::
29
ማይክ


30
ይሄን ደሞ የት ነው አምታውቲው?
በቀደም እነ ኤሚ አስተዋውቀውኝ ነው። ሌላ ነገር የለውም
31
ታዲያ ምናባቱ ሆኖ ነው! ባንድ ቀን ትውውቅ ሄኒ ምናምን የሚለው?
እሀ! እነ ኤሚ ሄኒ ስለሚሉኝ ነዋ
32
ጅኒ በያት!
አይ አንተ ደግሞ አበዛሽው። ምንድነው በሆነ ባልሆነው መነጫነጭ!
33
አይደለም እኮ ማሬ... ምን መሰለሽ.. እነሱን አታውቂያቸውም አገር ሁሉ የጠላቸው ዱርዬዎች እኮ ናቸው
አይ! በጣም በዛ! እኔ ህፃን አይደለሁም። የማደርገውን አውቃለሁ። በል አሁን ደክሞኛል ነገር አልፈልግም
34
እንዴ! ማሬ! አንቺ
35
ኤጭ አሁንስ በዛ!
ቻው! ነገ እንገናኝ። ደክሞኛል ብዬሃለሁ
36
ሄኒ ምን ሆነሻል! ፊትሽ ሁሉ ተቀያይራል።
37
አንቺን እኮ ነው ምንድነው የሆንሽው?
ምን እዚህ እንደ ክፉ ባል ይነዘንዘኛል።
ማ?
38
የኔ ታሪኩ ነዋ! አሁንማ በጣም አብዝቶታል። ጭራሽ ሰው ሰላም አይበልሽ ነው እንዴ?
አይዞሽ በቃ የኔ ቆንጆ! ለወንድ ሲበዛ ፊት መስጠት አያስፈልግም። በይ አሁን ተረጋጊ
ኒጃሳ! አሁን እንዴት ነው የሚጠናው?
TO BE CONTINUED...


ድብታ


ሄኖክ የዘካሪያስን HIV postive መሆን ከአወቀ ቀን ጀምሮ ተረብሿል።
1


2
ዘካሪያስ በኤች አይ ቪ መያዝ የማይታመን ነገር እኮ ነው!
ምን መሆናቸው ነው? ይህን ከመሰለ ፕሮግራም አቋርጠው እንዴት ዘፈን ይሉታሉ? አስቲ ቀይረው ጣቢያውን?


እኔን ይመክረኝ የነበረ የተረጋጋ ልጅ ፖዘቲቭ ከሆነ እኔ እንዴት ልተርፍ እችላለሁ!?
ወይ ጉድ! እንዴት እንዴት ነው የሚያረጋት አሁን በአሳት ውስጥ ዳንኪራ ምን ይሉታል!?
3



እኔ እኮ ገና በልጅነቱ ቤተሰቦቹ ለዩኝ አላዩኝ እያልኩ በአሳት ስጫወት ነው ያደኩት። ታዲያ እንዴት እተርፋለሁ?
4
አንተ ልጅ ምን ሆነሃል ሰሞኑን! አትሰማኝም እንዴ የምልህን? አጥፋ እኮ ነው የምልህ። ደሞ ብለህ ብለህ ዘፈን ታሰማኛ!?
ኧ...እሺ! አጠፋዋለሁ....ስላልሰማሁ ነው።


የሆነ ያልሆነውን እንዲህ እየከለከሉ...ወይ በስርዓት አያንጋግሩኝ... ዱርዬ አደረጉኝ።
አንተ ልጅ ሁኔታህ አላማረኝም። ምንድነው እንዲህ ፍዝዝ የሚያረግህ?
5
እዚህ ምንም ማረፍ አልቻልኩም አዲስ አበባ መመለስ አለብኝ።


ሄኖክ አዲስ አበባ ከተመለሰ በኃላም ድብርቱ አለቀቀውም።
6
ስልክህን አታነሳም እንዴ እኛ አንተን በመጠበቅም ፕሮግራማችን መፋለስ አለበት!?
አትጨክብኝ! silent ላይ ስለነበር አልሰማሁትም።


እንዴት ነው ሰሞኑን ስልክህንም አንተም silent ሆናችሁ ትዘልቀዋለህ? ሄኖክ ተው!
7
ህይወት አንዳንድ ጊዜ ዝምታም ያስፈልጋታል። ዝም ስትል ስለራስህ አጥብቀህ ማሰብ ትጀምራለህ።
ኧረ ፍልስፍና ከአዋሳ ዕረፍትህን ሳትጨርስ የተመለስከው ስለራስህ ለማሰብ ነዋ?!


ነገሩ ጉበቶኛል። ክፉኛ የምትፈልጭ መስሎሽ ከሆነ አትጨነቂ ምሳ፣ በርጫ ፣ ቀንጣሽ አጉራሽን ጨምሮ ጨብሲ ሳይቀር የክበር ስፖንሰራችን ዳንኤል አስፋው ነው።
8
ዳኒ እየጠበቀችን ነው። አንተን ጥሰንህ እንሄድም ብለን ነው አስካሁን የቆየነው ይልቅ ቶሎ እንውጣ!
እኔ አልሄድም። ...ተውኝ! አሁን ብቻዬን መሆን ነው የፈለኩት...


9
አንተ ደግሞ አታካብድ አዋሳ ሄደህ የሆንከው ነገር ካለም ትነግረናለህ።
10
ሄን እብደት ሲጀምር እኮ እንዲህ ነው የሚያደርገው።
ተውኝ! እኔ ስሞኑን የመዝናናት mood ላይ አይደለሁም አልሄድም አልኩዋችሁ።
ለራስህ ብለን ነው ድብርት አንቆ እንዳይደፋህ ዋ!
11
ከቆይታ በኃላ
ስድስት missed call!? እንዴት አልሰማሁትም?
Ok!.. ዘካሪያስ ደውሎ ነበር!...
12
ዘኪ እንደምን አለህ... መቼ ደውለህ ነው አልሰማሁትም እኮ እባክህ!?
ሃኪም ቤት ሆኜ ነው የደወልኩልህ።
13
በጣም አረፍ! ሃኪም ቤት ሄድክ?
የኔ CD 4 ስለቀነሰ አይተውልኝ መድሃኒት መጀመር አለብህ ስላሉኝ ልነግርህ ነበር።
14
ጥሩ ነዋ ታዲያ። ሀኪሞቹ ጀምር ካሉህ ጀምረ?!
እሱማ ምን አማራጭ አለኝ ብለህ ነው።ግን መድሃኒቱ አንዳንድ side effect አለው አለኝ ሃኪሙ እና አልገባኝም።
15
እስቲ ሃኪሙን እንደገና በደንብ ጠይቀው። እኔም 952 ደውዬ ቼክ አደርጋለሁ። ከቻልክ አንተም ደውል። ደግሞ ብዙም አትጨነቅ።
አሁን እንኳን እየቀለለኝ ነው። ይልቅ አንተን አጨናነኩህ መሰል!?
16
ኧረ እባክህ እንዲህ አታስብ የራሴ ጉዳይ አይደል እንዴ ይሄ?!
17
አላወክ ጭንቀት እና ስጋቱ ለአንተ ብቻ እንዳልሆነ።
18
ሄኖክ ከዘካሪያስ ጋር ከተሰነባበተ በኃላ።
ወይኔ ሄኖክ! ምንድነው የሚሻለኝ! ከአዋሳ ከመጣሁ ቀን ጀምሮ ካለ ኤችአይቪ ሌላ ነገር ማሰብ እኮ አቃተኝ።
19
ኤጭ! ምን ባደርግ ነው የሚሻለኝ?!
20
ሄኖክ ከቆይታ በኃላ በግተራ መጽሄት እያነበበ።
21
"...at risk for HIV" who me?
"Have I ever had unprotected sex?"
ኮንዶም ተጠቅሜ አውቃለሁ... እ... ግን ያልተጠቀምኩበትም ጊዜ ነበር?


22
ከቤቲ ጋር፣ እ፣ ከቃልኪዳን ጋር.... እ... ከማን ጋር ነው ደግሞ ያለኮንዶም የወጣሁት. ከሄራን ጋር ራሱ...ብለው!... ፍሪሀይወት፣ ሰሚራ...
23
"Is my partner HIV Negative?"
አይ...! እንኩዋን የሰው የራሴንም አላወኩ።
ሄኖክ የተኛቸውን ሴቶች ዝርዝር ሰማስታወስ እየሞከረ
24
25
ከስንት ሴት ጋር ነው እስከዛሬ የወጣሁት...? የሚገርም ነው!
እሺ ከዚህ ውስጥ ማን ማን ጋር ደውዬ ደህንነታቸውን ልጠይቅ እችላለሁ? እሺ መጀመሪያ የማን የማን ስልክ አለኝ?
26
ቆይ እሺ አምላል!...እ... እንደውም እሷ ጋር ልደውል
27
ምንድነው የምላት ግን!?
28
ምን አይነት ስራ ነው እየሰራሁ ያለሁት!? ቢቀርብኝስ እንዲህ ያለ ስለላ።
29
እንዳውም ወጣ ብዬ ዘና ብል ይሻለኛል።እረ ዲያ የምን አባቱ መጨናነቅ ነው?!
30
ምንድነው ሃሳብ
31
32
33
ምንድነው ሃሳብ ሁሌ-ጫ ገጭ ወደ ፍንም ጠላን አይቀርም ሞት አስቲ እንጫወት በሉ እንጂስት...
34
...የጭንቅ ቀኖች አይመሹም።
የሆንክ ሞጥሟጣ ነገር ነህ እሺ ቅድም ደብሮኛል ስትል አልነበር እንዴ ከምንጊዜው አፍ ለቀቀብህ?
እኔ እንጃ አንቺ ጉኔ ስትቀመጪ የሆነ ትልቅ ምላስ አፌ ውስጥ ጥልቅ አይል መሰለሽ!
35
ስሚ ይልቅ ትን አስኪልሽ መጠጣት ከፈለግሽ በጊዜ መውጫ ቁረጭ እና ብቻችንን ሆነን...
ተገኝቶ ነው? አንተን አራሱ አትጥኜ ብጠጣህ ደስ ይለኛል።


ሰካራም ዶሩሙ አይገባም...
36
እሺ ሲጃራ ማጨስ ከጀመርሽ ስንት ጊዜ ሆነሽ?
ውውይ! እኔ እሳው ጨዬት ውስጥ ብቀመቅም ይሻለኝ ነበር ምን ሆነህ ነው ጥያቄህ አስከረኝ::
የሰው ታሪክ ማወቅ ደስ ይለኛል:: ፅሃፊ መሆን እንደምፈልግ ነግሬሽ የለ?
37
ሰካራም አትሚዘዝ! ለሊት ተነስተህ ብቻ እስክርቢቶና ወረቀት ካላመጣሽ እንዳትለኝ... አመል ካለብህ በር ላይቆለፍ ገዝተህ ና!
እኔ ሂናክ እንዲህ ቅጥ ያጣ አመል እንኳን የለኝም...
38
ወንድ አይደለህ እንዴ::ወንድ ሲለክር ስንት አመል መለለህ ያለው:: ትፅፈዋለህ? ልንገርህ? ደራሲሲሲሲሲ....
በናትሽ እስቲ ንገሪኝ!?
39
ከየትኛው ልጀምርልህ? ከተማሪ፤ ከአስተማሪ፤ ከሃኪም፤ ከነጋዴ፤ ከላጤ፤ ከባለትዳር፤ ከቆንጆ... ከአልቃሻ፤ ከተደባዳቢ፤...
የሙያ ዝርዝር ንገሪኝ አልኩሽ? ቆይ ፍቅር ምናምን ይዞሽ ያውቃል?
40
ቀሽም ነህ አሺ! ለምን አይዘኝም... ባይገርምህ ስሞኑን ነው እሺ ከፍቅረኛዬ ጋር የተጣላሁት:: የሚያናድደኝ ከሱ ልጅ አለመውለዴ ብቻ ነው::
ልጅ መውለድ ትፈልጊያለሽ?
41
ጠራ ያለ ሰው ከተገኘ ምናለበት... አራስ ያሳድገዋል::እስቲ ስጠኝ ከጅኑ ልፈርፍለው...
ሃሳብና ጭንቀት ለመርሳት የጀመርኩት መጠጥ እኔ እራሴ የት እንዳለሁ አስረሳኝ እንዴ?
42
ይቺን ዘፈን አብረን እንዘፈናት?
43
44
45
አሳብሽ አሳቤ ተገጣጠመ አና
ሊገጣጠም ታየኝ አሳብሽ ካሳቤ
እሱዋም ከሳቡዋ እኔም ከአሳቤ
ሊገጣጠም ታየኝ አሳቢ ካሳቤ:
46
TO BE CONTINUED...

የቸገረው...




ፍለጋ
1
WOW! ይህን የመሰለ ዕሁፍ እስከ ዛሬ የት ተደብቆ ነበር?
2
ሴቶች ከወንዶች የሚጠብቋቸው 10 ነጥቦች... ቆይ ርዕሱ ይስተካከል። ማህሌት ከድንግሉ ሳሚ የምትጠብቃቸው ዋና ዋና አስር ነጥቦች
እስቲ አትጃጃል ላንብበበት!


3
የአራት ኪሎን ችክላ አላረፍሽውም አይ ደል? ፈተና ላይ እኮ ይሄ አይመጣም።
እና ዘና ማለት...ያለብኝም


4
እኛ ሲኒየሮች ብንዝናና ፈተና ጨርሰን ነው
በፎርመላ ሴቶችን ልታስደስት ትፈልጋለህ እንዴ? በዛ ላይ መዕሄቱ መቼ እንደወጣ እየው።
እኔ መቼስ ቢወጣ ምን ቸገረኝ! እስከጠቀመኝ ድረስ


5
ሴቶች ከወንዶች ብዙ ነገር ይፈልጋሉ። የምትሰጣቸው ግን አንድ ነገር ብቻ ነው
ምንድነው እሱ


6
ወንድነትሽን በቃ! ሌላ ተአምር የለውም።
ወንድነቱ ጠፍቶ አይደል የተቸገርነው?


7
ማህሌት ምን አፈልጋለሁ አለችሁ?... ልታስደንቃት ፈልገህ ነው?
ኧረ እሷ ምንም አትፈልግም።
ቆይ እሺ ለምንድነው ማህሌትን የፈራሃት? ንገረኝ እስቲ!


8
በቃ! ባለፈው ስደነግጥ አላበኝ እና በዚያ ሼም ያዘኝ።
በል በል ደውልና ቶሎ አማኞት ያለህ ትንፋሺ ሞቆህ ይሆናል።


9
መቆየት እየፈለግች አጣድፌ ይገርያት ወጣሁ እና በቃ...
በቃ ሳሚ ካኮረፈችሽ ተያት
10
ድሮም DC ትንሽ ተለማምደሽ ነው መሄድ የነበረብሽ።
ሴትኛ አዳሪጋ ? አይቀፍም በናታችሁ?
ኧረ አታካብድ... ትመርጣለህ! ጠዳ ጠዳ ያሉት አሉ።
11
ሳሚ DC ያለምንም ጣጣ መግቢያ መውጫውን ተምረሽ ወደኛ በኩንፊደንስ ትመጪያለሽ።
አንድ ጊዜ ባደርግ... ግን ምን አለበት? በተአምር!!
በማግስቱ፡ Cafe ሻይ እየጠጡ
12
ወይኔ... ደወለች
አንሳዋ ታዲያ ምን ያንዘረፍፍሃል?
13
ምን እላታለሁ? እባክህ ይቅርብኝ!
አምጣው ስልኩን እኔ አናግራታለሁ። ...እንዳውም አብረን እናገኛታለን።
14
15
አንተ ግን ምን አድርጌህ ነው? ዝም ብለህ ጥፍት ትላለህ?
ጥናት በጣም በዛ በናትሽ
እና ለኔ ስልክ መደወያ ጊዜ አጣህ? ነው እኔን ማግኘት አትፈልግም በጣም አዝናለሁ እሺ።
16
No! No! እንደዚያ አይደለም ስላልተመቸኝ ነው ።
እሺ አሁን የት ነህ? ላገኝህ እፈልጋለሁ
17
አሁን ወደ ቤት እየሄድኩ ነው። ስመለስ እደውልልሽና እንገናኛለን።
18
ካልደወልክ አልደውልም... እሺ....
ወንድ ሁሉ በቃ እንደተወደደ ሲገባው ለምንድነው ጥብርር የሚሉው?
አማራጭ
19
አንተ ቆይ በደንብ ለምንድነው ያላናገርካት?
ክዚያን ቀን ወዲህ I don't feel good
ቆይ እስኪ በደንብ ንገረኝ ምንድነው የሆንከው ያን ቀን?
አቦ ተወው! እሱን ቀን ማስታወስ አልፈልግም።
20
ለምን ቆይ? የሆነማ የደበቅከኝ ነገር አለ።
ምን እደብቅሃለሁ እ እ. በቃ እንሳሳም... ድንገት በቃ ለቀቅኩት...


ነዝሮሽ ነው ታዲያ ምን ታካብጃለሽ... ምንም ማለት አይደለም የመጀመሪያህ ስለሆነ ስሜታዊ ሆነህ ሊሆን ይችላል
21
አንተ የመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ ሆነህ ነበር?
እኔ እንኳን አላስታውስም። ጣጣ የለውም እየለመድክ ስትመጣ ስሜትህን መቆጣጠር ትጀምራለህ
22
የኔ ችግር ብቻ ይሆን እንዴ? እንዲህ እየሆንኩ እንዴት ነው የምለምደው?
በቃ እነዚያ የምትሏቸው ችኮች ጋር መሄድ አለብኝ
ነግሬሃለሁ እኮ እነሱ ገንዘብ ብቻ ነው የሚጠበቅብህ ከፈለክ ትጋብዛታለህ..በቃ!
23
24
ቤት ሄጄ ገንዘብ ነገር ላምጣና ነገ ለምን አንሄድም?
25
ደስ ይለኛል።
ፈለጣ
26
ጉሽ የኔ ልጅ እንዲህ ሊመችህ ቶሎ ቶሎ ብቅ ብትል ምናለበት?
ትምህርቱ ነው እንጂ እሱማ...
27
ለምንድነው የማትደውለው? እኔ ልደውልልህ ስሞክር ስልክህ አይጠራም።
Class ስገባ እያጠፋሁት ነው።
ፀጉርህ አድጐ ነው? ከሳ ብለሃል። ነው ምግቡ አልተስማማህም?
28
ኧረ እንዲያውም ኪሎ ጨምሬያለሁ።
29
አይንህ ብር ብሏል ልጅ... በል ሂድ አባትህ ጋር ተጫወቱ መጣሁ።
30
አይ ሳሚ አደግሽ ... ደሞ ቁመትሽ ምን አለለ?
ሳሎን አባቱ ጋ
31
አ... የሰፍትዌር መግዣ ፍራንክ ፈልጌ ነበር
ጐረምሳው? ምነው ባዘቦት ቀን? በደህና ነው ግን?


32
ምነው አንተ ልጅ ጣጣህ በረከተ? ትምህርት ነው ቀረጥ መሰብሰብ ነው የሚያስተምሩዋችሁ?
እንዲህ እያሸቆጠቆጠ እኮ ነው ፈሪ አርጦኝ የቀረው?
መች ጠይቂህ አውቃለሁ ከአሁን በፊት?
33
እኛ ለስንቱ እንሆናለን? ትምህርት ነው ጥርስህን ነክሰህ መማር ነው። ይህን የወጣቶቹን አንጉል ነገር ለመድክ?
እኔ ለትምህርት ነው የፈለኩት... ብዙም አይደለም...
ሳሚ ወንድሙ ክፍል
34
ይሄ የምደምረው ገቢ ብቻ እንዳይመስልህ ወጪም ነው። ደሞ ለእናንተው ነው የምለፋው...
እሺ ጨርስና እናወራለን።
35
ጐረምሳው! ዛሬ እንዴት ተከሰትሽ?
ችግር መውጫ መግቢያ አሳጥቶ ከግቢ አባረረኝ።
36
ምንድነው እሱ ወጪ በዛብሽ እንዴ?
...ፎቶ ኮፒው ምኑ... ምኑ...
37
አዩ... አልመሰለኝም ...ስጦታ ግብጣ... ምናምን እ!...
የጥናት ሰሞን ነው እኮ...
ይልቅ በደንብ አጥና በዛች ልጅ ፍቅር በኋላ ውጤትህ እንዳይበላሽ
38
አብሽር ደሞ ለጥናት!
39
እንዴት ሆናችሁ ግን ትገናኛላችሁ?
ምኑ?
በቃ አልተመቸኝም እባክህ።
ሁሉም ነገር
መውጣት ጀምራችሁ ነበር?
40
ያምሃል እንዴ!?
ያው የሚያጋጥም ነገር ነው ብዬ...ነው።
41
ብቻ ለማንኛውም ራስህን ጠብቅ!።
ማለት?
በበኩሌ sex ባትጀምር ደስ ይለኛል። ግን ከጀመርክ ወይም ልትጀምር ካሰብክ ኮንዶም ተጠቀም ማለቴ ነው።
42
ሽረ አብርሽ ታላቅ ወንድም ታላቅ ወንድም አያለ ነው
TO BE CONTINUED...

Discuss 'LIFE 101'

with your friends and your peers!

EDITION NINE

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ብሌን ከዮናታን ጋር ያላት የፍቅር ግንኙነት ደስተኛ ስላልሆነች ለተወሰነ ግዜ "break" እናድርግ ብላዋለች። አሁን ለደረሱበት ሁኔታ ምክንያቱ ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

2. ብሌን ለተወሰነ ግዜ እንለያይ ማለቷ በመሃከላቸው ለተፈጠረው አለመግባባት መፍትሄ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን? እናንተ የብሌን/የዮናታን ጓደኛ ብትሆኑ ምን ትመክሯቸዋላችሁ?

3. ማሬ የታሪኩ ሃይለኝነት እና እራት መጋበዝ ተደራርበው ወሲብ የማድረግ ግዴታ እንዳለባት እንዲሰማት አድርጓት ያለ ፍላጎቷ ከታሪኩ ጋር አድራለች። ይሄ ትክክለኛ አመለካከት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? አንድ ሰው ወሲብ መፈጸም ያለበት መቼና ለምንድነው?

4. ማሬ ከጓደኞቿ ጋር ጭፈራ ቤት ሄዳ ተደስታ መጥታለች። ስላሳለፈችው "አስገራሚ" ምሽት ለክፍል ጓደኛዋ ለሃይማኖት ስትነግራት ሃይማኖትም መዝናናቱ መልካም ቢሆንም አላማዋን እንዳትስት አስጠንቅቃታለች። ማሬ ግን ራሷን እና የመጣችበትን ግብ እንደምታውቅ ነግራታለች። ማሬ እንደምታስበው ለአላማዋ ትኩረት ሰጥታለች ወይ?

5. ሄኖክ የዘካሪያስን ኤች.አይ. ቪ. ፖዘቲቭ መሆን ካወቀ ቀን ጀምሮ ክፉኛ ደብሮታል። ስለራሱም አብዝቶ እየተጨነቀ ነው። ሄኖክ ጓደኛው ኤች. አይ. ቪ ፖዘቲቭ ስለሆነ ብቻ ይህን ያህል የተጨነቀበት ምክንያቱ ምንድነው? እናንተ በሄኖክ ቦታ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

6. ሄኖክ ከገባበት ድብርት ለመውጣት የወሰደው እርምጃ መጠጥ ቤት መሄድ ነበር። ከዛም ተከትሎ ባልተዘጋጀበት ሁኔታ ከሌተኛ አዳሪ ጋር አድሯል። እርምጃውን እንዴት አያችሁት? እናንተ እንደ ሄኖክ ድብርት ውስጥ ብትገቡ ምን ታደርጉ ነበር?

7. ሳሚ ከማህሌት ጋር ካጋጠመው ድንገተኛ ነገር ተነስቶ "ወሲብ ላይ ችግር ይኖርብኝ ይሆን?" የሚለውን ስጋቱን ለፍጹም አጫውቶታል። ፍጹምም ይሄን ችግር ለመቅረፍ መፍትሄው ወሲብ መለማመድ ለዚህም ቀላሉ አማራጭ ሌተኛ አዳሪ ጋር መሄድ መሆኑን ነግሮታል። ሳሚ ከማህሌት ጋር ላጋጠመው ችግር ወሲብን መለማመድ እና ማዘውተር መፍትሄ ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

8. ይሄ እርምጃ በሳሚ ህይወት ላይ የሚያስከትላቸው አደጋዎች አሉ? ከማህሌት ጋር፣ ከጤንነቱ እና ከስብእናው ጋር አያይዛችሁ ተወያዩ።

በዳጉ አዲስ የማይወራ ነገር የለም!

ጤናማ የፍቅር ግንኙነት ምን አይነት ነው?

ከወላጆቼ ጋር አራፍ ውይይት እንዴት ማድረግ እችላለሁ?

ወሲብ መጀመር ያለብኝ መቼ ነው?

ስራ ለማግኘት ምን ምን ነገሮች ማድረግ አለብኝ?

ከገርል ፍሬንዴ ጋር የፍቅር ጉዳዮችን እንዴት ማውራት እችላለሁ?

የቤት ውስጥ ስራ መስራት ያለብኝ እኔ ብቻ ነኝ?



በሸገር ኤፍ ኤም 102.1
ላይ ዘወትር እሁድ ከ8:30-9:00
እንዲሁም በድጋሚ ማክሰኞ ከምሽቱ 1:30-2:00
አብረን እንሁን!

CDC



VISIT US ON THE WORLD WIDE WEB!

For info on what the AAU MARCH Project is doing on campus go to:
www.aau.edu.et/march

For the most updated Information on HIV/AIDS in Ethiopia visit:
www.etharc.org

CALL 952 THE TOLL FREE HOTLINE TODAY!

Just dial 952 from any landline or mobile phone in the country and get your burning questions answered for free!

FOR ADDITIONAL INFORMATION ABOUT
THIS COMIC BOOK, PLEASE CONTACT:

ADDIS ABABA UNIVERSITY
MARCH PROJECT
P.O .Box 1176
Tel 251 (011) 1 248887
Email: aau_march@yahoo.com
Website: aau.edu .et/march

AIDS RESOURCE CENTER
MARCH PROJECT
AFRICA AVENUE
(BOLE ROAD), DEMBEL BUILDING
10th FLOOR
P.O. Box 26171code1000
Addis Ababa Ethiopia
Tel 251 (011) 5503584
Fax 251 (011) 5503749
Email: arc@etharc.org
Website: www.etharc.org









